# የረመዷኑ ሟርተኛ

ሐቢብ ሽረፋ- ከኡራኤል

እነሆ ቅዱሱ የረመዷን ፆም ሊገባ ከወር ያነሰ ጊዜ ብቻ ይቀረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ እያንዳንዱ ሙስሊም ምዕመን ራሱን ለአላህ ለማስገዛትና ነፍስያውን በጀነት ለማኖር ይፆማል፤ ይፀልያል። የተቸገሩትንም ያስባል፣ ካለው አካፍሎም ዘካ ያደርጋል፡፡ ታዲያ ይህን ቅዱስ ወቅት አንዳንድ ሃይማኖትን መነገጃ ያደረጉ ፖለቲከኞች ከተወሸቁበት ቦታ አቧራቸውን አራግፈው ብቅ እያሉ፣ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ከሌሎች የሃይማኖት ተከታዮች ወንድሞቹ ጋር በመከባበርና በመቻቻል አብሮ ይኖርበትን አስተሳሰብ በወሐቢያ ጉያ ውስጥ በመሸጉ አክራሪዎች አመለካከት ለመቀየር ደፋ ቀና እያሉ ነው፡፡

ለዚህ አባባሌ መነሻ የሆነኝ ሰኔ 8 ቀን 2004 ዓ.ም ለህትመት በበቃው ፍትህ ጋዜጣ ላይ “ረመዷንን ጠርጥሮ-ምርጫ በጓሮ” በሚል ርዕስ የቀረበውና “በጥንቆላ” የአጻጻፍ ስልት መንግስትን ለማጠልሸት የቀረበው ጽሑፍ ነው፡፡ ግለሰቡ በሦስተኛው ሀገራዊ ምርጫ (በ1997 ዓ.ም) ወቅት ህገ - መንግስትና ህገ - መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ በተደረገው የሀገር ውስጥ የተቀናጀ ዘመቻ በ“ተባባሪነት” የምናውቀው ጦቢያ መፅሔት ጋዜጠኛ የነበሩ ናቸው፡፡ በደርግ ቢለሚልነት የሚታወቁትን የመጽሔቱን አዘጋጆች ስራ በመደገፍ በይስሙላ ጋዜጠኝነት ሥርዓቱን በአመጽ ለማፍረስ የበኩላቸውን ጦር ሲወረውሩ እንደነበሩም የአደባባይ ምስጢር መሆኑ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም፡፡

መቼም እንደ አለመታደል ሆኖ አንድ ነገር ሀገራችን ውስጥ “ኮሽ” ባለ ቁጥር ካሉበት ጎሬ ተጠራርተው ብቅ በማለት “እነሆ የአመጽ ቀን መጣ!” በማለት የሟርት ናዳ የሚያዘንቡት እንደ አቶ ሁሴን ዓይነት “የጥንቆላ ነብዮች” ፍትህ ጋዜጣን የጥላቻ መጋለቢያቸው ካደረጉ ሰነባብተዋል፡፡ በጋዜጣው ላይ “ጋዜጠኛ ነበሩ” በሚል ስያሜ የቀረቡት እኚህ ግለሰብ፣ በሃሰት ቃላት የተሸሞነሞነው ጨለምተኛ እሳቤያቸው የሚያጠነጥነው፤ አብዛኛው ሙስሊም የሚከተለውን ነባሩን እስልምና በማጣጣል የሚመሩበትን የጽንፈኝነት አስተሳሰብ (ወሐቢያ) በሌሎች ላይ የአመጽ ጥሪ በሚመስል ሁኔታ ለማስተጋባትና በዚህም የእምነትና የሃይማኖት ነጻነቶችን መጻረረን እንደ ትክክለኛ ሃይማኖት አስመስለው ‘በማቅረብ ላይ ነው፡፡

እናም ይህን የግለሰቡን አጠቃላይ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በሌሎች ላይ የራሱን እምነት በኃይል ለመጫን የሚሻውን የወሐቢያን አስተሳሰብ እንደሚከተል አስመስለው ያቀረቡትን “የሃይማኖታዊ ንግድ” ዘገባን በመሞገት የበኩሌን ለማለት ብዕሬን ከወረቀት ጋር እንዲህ አገናኝቻለሁ፡፡

እንደሚታወቀው በኢፌዴሪ ህገ - መንግስትም ይሁን በተግባራዊ የመንግስት እንቅስቃሴ ውስጥ ሃይማኖትና መንግስት ለየቅል ናቸው፡፡ አንዱ በሌላኛው አሰራር ውስጥ አይገባም፡፡ ይሁንና አቶ ሁሴን እንደ ሌሎቹ አክራሪ የእምነቱ ተከታዮች (ወሐቢያውያን) ባልተጣራ ወሬ ላይ ተመርኩዘው (ለነገሩ አሉባልታ ካልያዙ በፍትህ ጋዜጣ ላይ ሊስተናገዱ አይችሉም) ‘መንግስት የሙስሊሙ ማህብረሰብን ምርጫ በጓሮ ሊያካሂድ ነው’ በማለት ከሰባት ዓመት በፊት ይመሩበት የነበረውን የነሲብ አጻጻፍ ዘዴ ዛሬም ላይ ገቢራዊ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡

መንግስት የሙስሊሙን ማህብረሰብ ትክክለኛ ጥያቄዎችን በመለሰበት ማግስት ምርጫውን ማካሄድ ያላባቸው የሃይማኖቱ ተከታዮች እንጂ፣ መንግስት አለመሆኑ ይታወቃል። እንደ አቶ ሁሴን ዓይነት ሁሌም ቢሆን በነሲብ የፈጠራ ወሬ ከላይ ወደታች የሚማስኑ ግለሰቦች ግን ሃቁን ለማየት የሚሹ አይደሉም፡፡ የሃይማኖት መሪዎችን የመምረጥም ሆነ የመሻር መብት የህዝበ - ሙስሊሙ ነው፡፡ የመንግስት አጀንዳ አይደለም፡፡

ፀሐፊው ይህን እውነት በመርገጥ "…ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባላረጋግጥም፣ መንግስት እንዲህ ሊያደርግ ነው የሚል ወሬ አለ" በማለት ያልተረጋገጠን ጉዳይ ወደ ሚዲያ ይዘው ለመቅረብ መሞከራቸው ግለሰቡ ከሃቅ ጋር ምን ያህል የተጣሉ መሆናቸውን የሚያሳብቅባቸው ነው፡፡ ለነገሩ እንዲህ ዓይነቱ ወፍ ዘራሽ ወሬን ማናፈስ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መንግስትን ለማጣጣል ማቄን ጨርቄን ሳይሉ በአሉባልተኞች መንደር ላይ ፎቶአቸውን በመለጠፍ የሚተዳደሩ ግለሰቦች ባህሪ በመሆኑ ብዙም የሚደንቅ አይሆንም፡፡

ይሁን እንጂ እንደ አቶ ሁሴን ዓይነት በሃይማኖት ስም ለመነገድ የሚፈልጉ ግለሰቦች "ሳይገድሉ ጎፈሬ፣ ሳያጣሩ ወሬ" እንደሚባለው ማህብረሰቡን ወደ አልተገባ ጽንፍ የሚመሩ ናቸው፡፡ ማህበራዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው ባለመሆናቸውም እጅና እግራችውን አንከርፍፈው ያለምንም ይሉኝታ የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማሳካት አመጽን ከመቀስቀስ ወደ ኋላ አይሉም (በምርጫ 97 ወቅት ጦቢያ ጋዜጣና መጽሔት ያከናወኑትን ፀረ - ህገ -መንግስታዊ ተግባር ያስታውሷል!) እናም የዛሬው በጥርጣሬ የታጀለ ጽሑፋቸው ከዚሁ እምነታቸው የመነጨ ለመሆኑ ጠቢብ መሆን የሚያሻው አይመስለኝም፡፡

ግለሰቡ በነካ የቅጥፈት እጃቸው አብዛኛው ሙስሊም ማህበረሰብ ነባሩን እምነት በመቃወም ወሐቢያን የሚከተል መሆኑን ያለ ሃፍረት ጽፈዋል፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን አብዛኛው የሀገራችን ሙስሊም ከክርስቲያን ወንድሞቻችን ጋር በመቻቻልና በመከባበር ለዘመናት የኖርንበትን ነባር እምነት የሚያከብር እንጂ፣ የክርስቲያኖችን ህገ - መንግስታዊ መብት በመጋፋት የግድ ሙስሊም ሁኑ በማለት በሸሪዓ ህግ የሚተዳደር መንግስትና ሀገር እንዲኖር የሚሻው ወሐቢያ ተከታይ አይደለም፡፡ እርግጥ ወሐቢያን እንደ ፖለቲካዊ ግብ የሚቆጥሩ ጥቂት የአስተምህሮቱ ተከታዮች ቢኖሩም፣ እነዚህ ኃይሎች ከሃይማኖታዊ እሳቤያቸው ይልቅ የስልጣን ጥም ያቃጠላቸው በመሆናቸው፣ እንኳንስ አብዛኛውን ሙስሊም ሊወክሉ ቀርቶ ራሳቸውንም ቢሆን በወጥ አቋም የሚመሩ አይደሉም፡፡

'ይህን እውነታ መስማት የማይፈልጉትና በጽሑፋቸው በእነዚህ ኃይሎች ጎራ የሚመደቡት አቶ ሁሴን ግን የሌለ ነባራዊ ሃቅን ከህልማቸው ሰነድ እየመዘዙ እንዲህ ለማለት ይዳዳቸዋል፡፡… "በፊት የነበሩት ባህሎች፣ ወጎች፣ ደንቦችና ሥርዓቶች ዛሬ እየተለወጡና እየተሻሻሉ በአዳዲስ እየተተኩ መጥተዋል፡፡" … ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ሃይማኖት በሆነው እስልምናችን ውስጥ የተለወጠው ምን ዓይነት ስርዓት ነው? ተብለው ቢጠየቁ ምላሽ የማይኖራቸው ፀሐፊ ተብዬ፣ የጽንፈኝነትና የአክራሪነት ዋሻ የሆነው ወሐቢያ አስተሳሰብ ተከታይ ስለሆኑ ብቻ ነባሩን እስልምና ለማጣጣል የተጠቀሙበት አመክንዮ ግልብ ስሜት ከመሆን የሚዘል አይመስለኝም፡፡

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላለፉት 21 ዓመታት ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ተከትለው፣ ወንድም ከሆነው የክርስትና እና የሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር እጅና ጓንት ሆነው እንዲሁም በክፉውም ሆነ በደጉ ወቅት “አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ” ተባብለው ኖረዋል፡፡ ህገ - መንግስቱ በሰጣቸው መብትም ሃይማኖታቸውን አክብረው የሌሎች ሃይማኖትም እንዲከበር አድርገዋል፡፡ በዚህም እንደ ዜጋ በሀገራቸው ሁለንተናዊ ጉዳዮች ውስጥ በእኩልነት በመሳተፍ ጥቅሞቻውን ማረጋገጥ ችለዋል፡፡

ነገር ግን የወሐቢያውን መንፈስ በጽሑፍ ለማንገስ የሞከሩት ግለሰብ “…በቀድሞ ዘመናት ያለ ዕውቀት ይሰሩ የነበሩ ሃይማኖታዊ ተግባራት አሁን በዕውቀት እየተተገበሩ ናቸው” ማለታቸው ከቶ ምን ማለት ይሆን? … አብዛኛው የሀገራችን ሙስሊም በአሁኑ ወቅት እየተገበረው የሚገኘው በነባሩ እምነት አማካኝነት መቻቻልን፣ መተሳሰብን፣ ሀገራዊ አንድነትን የፈጠረ አስተሳሰብ ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት የአንድ ስልጡን ማህበረሰብ ዴሞክራሲያዊ እሳቤዎች እንጂ፤ ያለ ዕውቀት የተከናወኑና በመተግበር ላይ የሚገኙ አይደሉም፡፡

እርግጥ በአቶ ሁሴን የሃሰት መዝገበ - ቃላት ፍቺ መሰረት እነዚህን ተግባራት በዕውቀት መተግበር ማለት፤ አለመቻቻል፣ አለመተሳሰብ፣ ሀገራዊ አንድነት አለመፍጠር ከመሆን አይዘልም፡፡ ይህ ደግሞ በእርሳቸው አዲሱ እምነት (ወሐቢያ) አስተምህሮት ሊሆን ይችላል፡፡ ታዲያ የእርሳቸው ወሐቢያ እምነት ይኸው ከሆነ፤ ተግባሩ ለሃይማኖታችንም ሆነ ለሀገራችን የሚበጅ አይደለም– እሳቤው የሸይጣን  እንጂ የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ባለመሆኑ፡፡

እናም በየትኛውም ማህብረሰብ ውስጥ ጥላቻን እና አለመቻቻልን የሚሰብክ ሰው ተግባሩ ሃይማኖታዊ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ ምክንያቱም እስልምናም ይሁን ክርስትና ለአማኞቻቸው ፅድቅን የሚያስገኙ ተግባራትን የሚያከናውኑ እንጂ፤ ብጥብጥንና ሁከትን በመፍጠር ምድራዊ ስልጣንን ለማግኘት በሚቋምጡ ባለመሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም የአቶ ሁሴን ነባሩን እምነት በማጣጣል ወሐቢያን የማንቆለጳጰስ አባዜ ጥንስሱ ፖለቲካዊ ፍላጎት እንጂ ሃይማኖታዊ ማንጸሪያ የሌለው መሆኑን ለመገንዘብ ምርምር የሚያስፈልገው አይመስለኝም፡፡

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ እንደ ፍትህ ጋዜጣ ፀሐፊው ዓይነት ግለሰቦች ፅንፈኝነትን አጥብቀው የያዙ በመሆናቸው የማንኛውንም ግለሰብ መብት አያከብሩም፡፡ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ እና በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲፈቱ አይፈልጉም፡፡ ጥላቻንና መናቆርን የፍላጎታቸው ጉዳይ ማስፈጸሚያ አድርገው ይጠቀማሉ፡፡ የመንግስትና የሃይማኖት መለያየትን ህገ - መንግስታዊ አጥር በማፈረስ በማን አለብኝነት እምነታቸውን በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ በኃይል ለመጫን ይራወጣሉ፡፡  ለዚህም ነው ቀደም ሲል በመግቢያዬ ላይ በጠቀስኩትና አቶ ሁሴን “ረመዳንን ጠርጥሮ - ምርጫን በጓሮ” የሚል ተረት - ተረት በማሰማት የምናብ ፍላጎታቸውን በሚዲያ  አማካኝነት እንደ መርዝ ለመርጨት  የፈለጉት ፡፡

ምንም እንኳን የረመዳኑ ሟርተኛ ግለሰብ ያሻቸውን ቢሉም፤ ዜጎች ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን ተከትለው የሚፈልጉትን ዓይነት እምነት መምረጥ እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፡፡ ነባሩንም ይሁን ጽንፈኛውን ወሐቢያን የመምረጥ መብት የሙስሊሙ ማህበረብ እንጂ፤ የመንግስትም ሆነ እንደ አቶ ሁሴን ያሉ

“ሃይማኖታዊ ነጋዴዎች” ጉዳይ አይደለም፡፡ ይሁንና በዜጎች መካከል ሃይማኖት ነክ ችግር ሲኖር ብሎም መንግስትን በማዳከም የሸሪዓን አስተዳደር እንመሰርታልን የሚሉ ፀረ - ህገ - መንግስታዊ ሃሳቦች ሲንሸራሸሩ መንግስት እጁን አጣጥፎ እንደማይቀመጥ ማስተዋል ያሻል፡፡

ጥቂት ጽንፈኞች ነባር የእስልምና ተቋማትን ለማፍረስ እንዲሁም የእምነቱን ተግባሮች በነጻነት እንዳይፈጽሙ ሁከት የመፍጠር እንቅስቃሴዎች ሲኖሩ፣ ህግና ስርዓትን የማስከበር ኃላፊነት ያለበት መንግስት ድርጊቱን ለማስቆም መስራቱ አይቀርም፡፡ ከዚህ ውጭ በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ በመግባት እምነትንም ይሁን የሃይማኖት አባቶችን የመምረጥም ሆነ የመተቸት መብትም ይሁን ፍላጎት የሌለው መሆኑን የረመዷኑ የአመጽ ሂርተኛ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

ለ13 ዓመታት በጋዜጠኝነት መስራታቸውን፣ ነገር ግን ከሙያው ጋር በሚጣረስ ሁኔታ “እንዲህ የሚባል አሉባልታ ሰምቼ ጻፍኩ” በማለት ያለ አንዳች ሃፍረት ሃሰትን ለመደረት የፈለጉት እኚህ ግለሰብ፣ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ እውነተኛ ፍላጎታቸውን አንጸባርቀዋል፡፡ ግለሰቡ እንደምን የአጠቃላዩ ሙስሊም ወኪል እንደሆኑ ለማንም ግልጽ ባይሆንም፡፡ “... የኢትዮጵያ ሙስሊም መንግስት እንደሚፈልገው ‘በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች’ ተብለው እንዲጠሩ አይፈልጉም...” በማለት ያሰፈሩት አባባል ትክክለኛ ፍላጎታቸውን አመላካች ይመስለኛል፡፡

ምንም እንኳን አቶ ሁሴን ጥቂቶቹን የወሐቢያ አስተምህሮት አራማጆችን እንጂ አብዛኛውንና ነባሩን የእስልምና እምነት ተከታይን ባይወክሉም፣ ጥቂቶች የሚከተሉት ና የወከሉት የእምነት ክፍል ‘በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች’ ተብለው መኖር እንደማይፈልጉ እየነገሩን ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት፣ ይህ እውነታ እርሳቸው የሚወክሏቸው ጽንፈኞችና አክራሪዎች እንደ ማንኛውም ዜጋ ‘ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች’ መባል ካልፈለጉ፣ የራሳቸውን እምነት በሌሎች ላይ በጉልበት በመጫን በሸሪዓ የሚተዳደር መንግስትና ሀገርን የሚናፍቁ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

ምክንያቱም የግለሰቡ አገላለጽ ‘መባል ያለብን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች ሳይሆን፣ የሙስሊም ሀገር ዜጎች ነው’ የሚል አንድምታ ሰላለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ “ሃይማኖታዊ መንግስትም ይሁን መንግስታዊ ሃይማኖት አይኖርም” ተብሎ በተደነገገባት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራ አይለደም፡፡ አስተሳሰቡም በቀጥታ ከህገ - መንግስታዊ ሰርዓቱ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ለምን ቢባል፣ የክርስቲያን መንግስት እንደሌለው ሁሉ፣ የእስልምና መንግስት በዴሞክራሲያዊቷ ሀገራችን ውስጥ ሊኖር ስለማይችል ነው፡፡ ይሁንና ግለሰቡ “ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም’ እንደሚባለው ሆኖባቸው በቅንጅት ወቅት በጋዜጠኝነት ስም በተባባሪነት እንዳደረጉት ‘ህገ -መንግስቱን መናድ ለእኔ አዲስ አይደለም’ የሚሉ ከሆነ ምርጫው የእርሳቸው ስለሆነ ልከራከራቸው አልሻም፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ አቶ ሁሴን ነባሩን የእስልምና አስተምህሮት አምርረው የሚጠሉበት ምክንያት “አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ” እንዲሉት ዓይነት ያፈጠጠና ያገጠጠ ሃቅ ያለው ነው፡፡ ይኸውም ነባሩን እስልምና የሚከተለውን ሙስሊም በማደናገር የምርጫውን ሚዛን ለማሳት የታለመ ሴራ ነው፡፡ነባሩን የመቻቻልና የመከባበር እምነትን በመደፍጠጥ በአዲስ የጽንፈኝነት አስተሳሰብ ለመተካት የሚደረግ ሩጫም

ለመሆኑ የረመዷኑን ሟርተኛ ግለሰብን “… ቀድሞ ይሰሩ የነበሩት ነገሮች መተው ጀመሩ፡፡ ይህ አክራሪነት፣ አሸባሪነት አልያም አዲስ እስልምና መጣ አያስብልም” የሚል ዲስኩር መጥቀስ ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡

ግና ለጽንፈኝነት ኑባሬ ናፍቂው ግለሰብ ‘ቀድሞ ይሰሩ የነበሩ ነገሮች መተው ጀመሩ’ ማለት ከቶ ምን ይሆን? …እኔ እስከማውቀው ድረስ በሃይማኖቱ ውስጥ ቀደም ሲል የነበሩት ክንዋኔዎች እስላምና ክርስቲያን ሳንባባል በፍቅር ማዕድ መቁረሳችንን፣ አንዳችን የሌላችንን የእምነት ቦታዎች አክብረን መኖራችንን፣ በእስላማዊም ሆነ ክርስቲያናዊ በዓላት የሁለቱም አማኞች የእንኳን አደረሳችሁ መልካም ምኞት ከመለዋወጣቸውም በላይ በመጠራራት ቤት ያፈራውን አብረው በመቋደስ በዓላትን በጋራ የሚያከብሩበት ሁኔታ የምንከራበት እሴታችን ሆኖ ዘመናትን ያስቆጠረ አንዱ የአብሮነታችን መገለጫ በመሆኑ የምንከራበት ነው፡፡

ይሁንና በሀገራችን ውስጥ የአክራሪነት አስተሳሰብ ብቅ ጥልም እያለ ሲከሰት የተፈፀሙት ተግባራት ከዚህ የአኗኗር ዘይቤያችን በእጅጉ ያፈነገጡ ሆነዋል፡፡ እስቲ ጥቂት አብነቶችን ላንሳ፡፡ …በሀገራችን ውስጥ በእስልምና እምነት ስም የሚንቀሳቀሰው “ካዋርጅያ” የተሰኘ ፀረ - ህገ - መንግስት ቡድን መስጂዶችንና መካነ - መቃብሮችን አቃጥሏል፡፡ እንደሚታወቀው ከዚህ ቡድን በተለየ አቋሙ የተገነጠለው ወሐቢያ ዕውቀትን ለመሻት ካለው ፍላጎት በስተቀር በሌሎች ተግባሩ ከካዋርጅያ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ነው፡፡

ወሐቢያ ማለት ይኼ ከሆነ ደግሞ፤ እንኳንስ የሌላውን ሃይማኖት ሊያከብር ቀርቶ የሙስሊሙን ህብረተሰብ ነባር ሃይማኖታዊ ቦታዎችን ሳይቀር የሚቃወም ለመሆኑ መገመት አይከብድም፡፡ ምናልባትም አቶ ሁሴን በጽሑፋቸው ላይ ‘ስለምን የአሜሪካ መንግስት ነባር የእምንት ቦታዎች ያድሳል፤ ቅርሶችን ይንከባከባል?’ በማለት የሚከራከሩት የአስተሳሰባቸው የዘር ሐረግ የሚመዘዝበት ካዋርጅያን እያስታወሱን ይሆን እንዴ?– ግና እውነታውን የሚያውቁት እርሳቸውና ‘ወዳጆቼ ናቸው’ ያሏቸው ጽንፈኞች ብቻ ናቸው፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፤ እንደ ሳዑዲ አረቢያ እና ባህሬንን በመሳሰሉ ሀገሮች ውስጥ ስር የሰደደውን የወሐቢያን አስተሳሰብ ብንመለከት፣ ሃይማኖትና መንግስት አንድ መሆን አለባቸው የሚል አቋም እንዳለው እንገነዘባለን፡፡ በጎረቤታችን ሶማሊያ ውስጥ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት የሚታትረው አሸባሪው አል - ሸባብም ከፊል ጎኑ ለዚህ ጽንፍ የቀረበ መሆኑ ይነገርለታል፡፡ እርግጥ እያንዳንዱ ሀገር ከራሱ ነባራዊ እውነታ በመነሳት የፈለገውን የመንግስታዊ ስርዓት አወቃቀር ሊከተል ይችላል፡፡ በርካታ ሃይማኖቶች ያሉባት ሀገራችን ግን ለዚህ ዓይነቱ የወሐቢያ የሸሪዓ አስተዳደር ፍላጎት ቦታ የላትም፡፡ ምክንያቱም ሃይማኖታዊ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደማይኖር የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነው የሀገሪቱ ህገ - መንግስት በግልጽ በመደንገጉ ነው፡፡

እንግዲህ እነ አቶ ሁሴን በአሉባልታ ፈረስ ሽምጥ እየጋለቡ የሚያቀነቅኑለት ወሐቢያ (አዲሱ እምነት) ግቡ ሃይማኖታዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ስልጣንን መቆናጠጥ ለመሆኑ አስረጅ የሚያሻው አይመስለኝም፡፡ለምን ቢባል፤ የእምነቱ አሳቤዎች ባሉባቸው ሀገራት የሚያከናውነወን ተግባር እንዲሁም

የፍትህ ፀሐፊው ግለሰብ ዘወርዋራ በሆነ መንገድ ‘የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እየተባልን መቀጠል አንፈልግም’ በማለት ዓላማቸው የሙስሊም ሀገር እንዲኖር መሻት መሆኑን በገደምዳሜውም ቢሆን ጨረፍ አድርገው ስለነገሩን ነው፡፡

ምንም እንኳን ግለሰቡ ስለ ሙስሊሙ ምርጫ በተጣባቸው የአሉባልታ ተውሳክ ሊጠረጥሩት ቢሞክሩም፤ መንግስት የመረዱን ፆም በሠላም ገብቶ እንዲወጣ መንግስታዊ ተግባሩንና ኃላፊነቱን እንደሚወጣ ቢረዱት የሚበጅ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ በተረፈ በቅዱሱ ፆም ሟርትን እያስቀደሙ የአብዛኛውን ህዝበ ሙስሊም ፍላጎት በአክራሪ “ወሐቢያዊ” ናፍቆተ - አመፅ እሳቤ የአብዛኛውን ሙስሊም እምነት መሸርሸር እንደማይቻል ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ማንኛውንም ዓይነት ምርጫ እንደ ቅንጅት ወቅት በአመፅ ከአብዛኛው ህዝብ እጅ ለመንጠቅ መሻት ጊዜው ያለፈበት ተራ የፖለቲካ ስልት ነውና።